የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ሰኔ 2/1999 (ጁን 9/2007)

## የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ጠቅላላ ስብሰባውን አጠናቀቀ

## አዲስ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴና የቅርንጫፍ መሪዎችም ሰየመ

ከተመሰረተ 12 ዓመታትን ያሳለፈው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ) ሰኔ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. ጠቅላላ ስብሰባውን አካሂዶ አዲስ የስራ አስኪያጅ ኮሚቴን ሰይሟል፡፡ በዚህ ስብሰባ በርከት ያሉት ቅርንጫፎቹ ተካፋይ ሆነዋል፡፡

የኢፖእአኮ ጠቅላላ ሰብሰባ ሰፋ ባለ መንገድ የተወያየባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው---

- ያለፉት ዓመታት የኮሚቴው እንቅስቃሴና ያስመዘገባቸው ውጤቶችና ያጋጠሙት ችግሮች፤
- በካናዳ ቅርንጫፍ ሁለት አባላት የኮሚቴውን ህግ በመጣስና ራሳቸውን ከኮሚቴው ማዕከል በማግለል የተሰማሩበት መስመር እያስከተለ ያለው ችግርና ውዥንብር፤
- በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብት መጣስ መፋፋሙና ይህንንም በተመለከተ ኮሚቴው ሊያደርግ የሚገባው የማጋለጥ እንቅስቃሴና ወደፊት ተግባሮቹ በዝርዝር፡፡

ስብሰባው በእነዚህና በሌሎችም ጥያቄዎች ላይ በስፋት ተወያይቶ በምስረታው ሰነድ በተገለጠው መሰረት ኮሚቴው አሁንም ትኩረቱን በተረሱ እስረኞችና ባልተጋለጡ የመብት ረገጣዎች ላይ ማድረጉን እንዲቀጥል ስምምነት ተደርሷል፡፡ ኮሚቴው በቆራጥነት ላለፉት 12 ዓመታት ያካሄደው ትግል የሚመሰገን ቢሆንም ዛሬ ከፊቱ ተደቅነው ካሉ ችግሮች አንፃር ገና ብዙ መስራት እንዳለበትም ታይቷል፡፡ ኮሚቴውን ለማፍረስ ሆነ ለማዳከም ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የተካሄዱት ዘመቻዎች የታወቁ ሲሆን ይህን ሁሉ ተወጥቶ መቀጠል መቻሉ በአባላቱና በደጋፊዎች ፅናት መሆኑም ተጠቁሟል፡፡ በካናዳ ያለው ቅርንጫፍ ራሱን ከማዕከሉ በማግለልና በዚህና በሌሎችም አቅዋሞች የኮሚቴውን ህግና አሰራር በመፃረር መቀጠሉንና የማዕከሉንም ማሳሰቢያዎች ምላሽ መንሳቱን ስብሰባው ተገንዝቦ ለካናዳው የኮሚቴ ቅርንጫፍ በህጉ መሰረት አዲስ ሃላፊ መድቧል፡፡ ይህንን ውሳኔም የሚመለከታቸው እንደሚያከብሩ ያለውንም ተስፋ ገልጧል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ የሕዝብን ሰብዓዊ መብት በአስከፊ ደረጃ እየረገጠና ህዝብን እያሰቃየ መሆኑን የተወያያው ጠቅላላ ሰብሰባ ይህን ሁኔታ በማጋለጥና ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት መከበር ደጋፍ ለማስገኘት ኮሚቴው እንቅስቃሴውን ማጠናከር እንዳለበት አምኖበታል። በዚህም ረገድ የኮሚቴው ድህረ ገፅ ብዙ ሺዎች የሚያዩት ቢሆንም ይበልጥ ስራውን እንዲያስፋፋ ያስፈልጋል ተብሏል። የእስረኞች ወይ ሰማዕት ቤተሰቦችን የመርዳቱም ጥረት እንዲስፋፋ፤ ሌሎች ቅርንጫፎችም እንዲከፈቱ ወዘተ በሚል የወደፊት ተግባሮችም ተወስነዋል።

የሰኔ 2 ኡ ጠቅላላ ስብሰባ የሚከተሉትን በስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባልነት መድቧል።

1. ዶክተር ገላዬ ታደሰ ሊቀመንበር (soceppaustralia@yahoo.co.au)
2. ተሻለ ተስፋዬ ም/ሊቀመንበር ( soceppca@yahoo.com)
3. ዘመድኩን ለማ ፀሐፊ (secretary@socepp.de)
4. ዘወልደ እንግዳ ገንዘብ ያዢ ( treasurer@socepp.de)
5. ጌዴዮን ተስፋዬ ዜና ክፍል ( info@socepp.de )

የሚከተሉትንም የቅርንጫፍ ሃላፊዎች መድቧል--

ዮናስ ግርማ -- የሰሜን አሜሪካ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር ( soceppna@yahoo.com)

ተሻለ ተስፋዬ -- የካናዳ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር ( soceppca@yahoo.ca)

ሱልጣን አሊ --የዴንማርክ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር (soceppdenmark@yahoo.dk)

ጌዴዮን ተስፋዬ -- የጀርመን ቅርንጫፍ ሊቀመንበር (info@socepp.de)

መኮንን ቅጣው --- የሆላንድ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር (soceppholland@yahoo.com)

ባዩ ቦጋለ --- የእንግሊዝ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር (soceppuk@yahoo.co.uk)

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት እንዲከበር የጀመረውን ትግል እንዲቀጥልና እንዲያጠናከር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሙሉ ድጋፉን በመስጠት እንዲያግዙት ጥሪ ያስተላልፋል።

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE